# ወሬ ነጋሪው

የመጽሓፉ ርዕስ - ወሬ ነጋሪ

ደራሲው - መሃመድ ይማም

ትችት - አብርሃም በየነ

ሰው ከኖረ ከሚስቱ ይወልዳል የሚል አባባል ሳትሰሙ አትቀሩም። አባባሉ እኔን የሚያስገርመኝን ያክል እናንተንም ያስገርማችሁ እንደሁ ግን አላውቅም። ዘወትር አባባሉን ስሰማ እኔን ግን ሰው ከሚስቱ ያልወለደ ከሌላ ከማን እንዲወልድ ቢጠበቅበት ነው ተረቱ የተተረተው? እንድል ያስደምመኛል። በዚህ አባባል ዙሪያ አበው የቋጠሩት ቁምነገር መኖሩን ግን አልጠራጠርም። እናም አባብሉን ከአንዳንድ ገጠመኞች ጋር አገናዝበውና ይህን ያበውን ጥልቅና ጥበባዊ እሳቤ ሸብ አድርጌው ሳልፍ መስተጋብሩ በራሱ ያስገርመኛል። ግርምት የዕይታ የሽፋን ቆዳ ነው። በውስጡ እውነቱንና ውሸቱን የሸፈነበት ዱባብ። ሲገልጡት ብዙ ትዝብት የሚታይበት። እንደ መሃመድ ይማም "ወሬ ነጋሪ"።

## ወሬ ነጋሪ ማለት ምን ማለት ነው?

ከዘመድ አዝማድ እርቀን የምንኖር ሰዎች ከብዙ ቆይታ በኋላ ስንገናኝ ሰላምታ እንደተለዋወጥን ቀጣዩ ጭው ውታችን የሚሆነው ስለቤተሰብና ስለ ሀገር ይሆናል። የቤተሰብ ወሬ ታገኛለህ? አገር ቤትስ ምን ወሬ አለ? እየተባባልን እንጠያየቃለን። የምንጠብቀው ወሬ ግን እውነትም ውሸትም ሊሆን ይችላል። ወሬውን የሚነግረን ሰውም ወሬውን ሲያመጣልን የሰማውን ወይም ያየውን ሊሆን ይችላል። ይህ የወሬ ነጋሪ አንደኛው ገጽታው ሲሆን ሌላም ገጽታ አለው።

ለወሬ ነጋሪ አንድም ሰው ሳይተርፍ ቀረ ማለትም ሌላው የወሬ ነጋሪ ትርጉሙ ሊሆን ይችላል። ወይም እንደ መሃመድ ይማም ሁሉም ሰው አልቆ ለወሬ ነጋሪ የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ ለማለትም ይሆናል። ዘበተኛ፤ ውሸታም፤አሉባለተኛ ማለትም ይሆናል። እንደ ቃሉ አጠቃቀም። በዚህም በሉት በዚያ ወሬ ግን በወሬነቱ ወሬ ከመሆን ያለፈ ትርጉም አይኖረውም። የሆነው ሆኖ ግን መሃመድ ይማም ለመጽሃፉ ርዕስ መርጦታል። ያውም የኢሕአፓን ልሳን ዴሞክራሲያን ጠቅሶ። ሰው ከኖረ ከሚስቱ ይወልዳል ይሏችኋል ይህ ነው።

መሃመድ ከማዕከላዊ ኮሚቴ ስልጣን ሁለት እርከን ዝቅ ብሎ በዞን ኮሚቴ ስልጣን የነበረው የአመራር አባል ነበር። የጎሕ መጽሔት አዘጋጅም ነበር። ጎሕ የላይላ ካሊድን ጀብዱ፤ የሮዛ ሉክሰምበርግን ቁርጠኝነት፤ የአንጀላ ዴቪስን አብዮታዊ ትግብርቶች በቱሉ ፎርሳ ትርክት አንበርክካ ብዙ ታጋይ ማርካ ነበር። በአብዮቱ ሲርመጠመጥ የነበረውን ወጣትም በጃሌ ቢያና በሳቱ ተሰማ ስንኞች ራሷን አጅግና ሌላውንም አጀግና ነበር። ጀብድን በጀብዱ ያስንቅ ዘንድም በብዕር ሚዶ የወጣቱን አዕምሮ የነቀሰች መጽሔት ነበረች። የጎሕ መጽሄት አዘጋጅ የነበረው መሃመድ ይማም ግን ከአርባ ዓመት ቆይታ በኃላ ፈሪ ነበርኩ እንዳውም ቡከን ሲለን ለማመን እንቸገራለን። ትናንት ያልነበረውን ፍርሃት ዛሬ ተከናንቦ እንድናየው ተጨፈኑና ላሞኛችሁ ሲለንም አንባቢዎቹን የናቀን መሰለኝ።

ፍርሃት በማንኛውም ሰው ውስጥ የሚኖር የሰው ልጆች ባህሪይ ነው። ደፋር የሚባለው ፍርሃቱን መሸሸግ የቻለ ብቻ ነው። መሃመድ ደፋርም ፈሪም ነበር ብለን እንመን። ድፍረቱን ከጅማው ንግግሩና ከጎሕ መጽሄት ምንጮቹ ልንቀዳው እንችላለን። ፍርሃቱንም ከአንጃዎቹ ክህደትና ክህደቱን ተከትሎ ከመጣው መገዳደል ጋር ልናያይዘው እንችላለን። ከዚህ በኋላ የመሃመድ ፍርሃት በመጠጥ ዋሻ ውስጥ መሸሸግ ጀምሯል። የሚገርመው ነገር ግን ዛሬም በስጋት መኖሩ ነው። መሃመድ ድሮውንም ፈሪ ቢሆን ኖሮ አይደለም ለዞን ኮሚቴ አመራር ቀርቶ ለህዋስ መሪነት እንኳ አይመረጥም ነበር።

በዚያን ወቅት በኢህአፓ ለመመልመል አንደኛው መስፈርት ቆፍጣናነት ነበር። ዕጩው አባል ብሩህ አዕምሮ ያለው፤ አመኔታ የሚጣልበት፤ ባህለ-ብልሹነት የማያጠቃው፤ ዝርክርክ ያልሆነ፤ ልበ-ሙሉና በራሱ የሚተማመን መሆኑ ተገምግሞ ነበር ለአባልነት የሚታጨው። መሃመድም ከሞላ ጎደል እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ መሆን አለበት በህዋስ ሊታቀፍ የቻለው። እርሱ ግን ሊያሳምነን የሚሞክረው ቡከንና መሸተኛ (alcoholics) መሆኑ እየታወቀ ነው በኢህአፓ የታቀፈው። ወሬ ነጋሪ ዕውነትም ወሬ መሆኑ የሚታወቀው እዚህ ላይ ነው።

ኢህአፓ እንደ ወገራ አፈር የሰጡትን አዝዕርት የሚያበቅል ድርጅት ነበር። የወገራ መሬት ከሚያዚያና ግንቦት ወራት በቀር ዓመት እስከ ዓመት ሁሉንም የሰብል ዓይነቶች ያዘምራል። ወገብ የሚያሸመደምደውን ጓያን ጨምሮ።

ሽንብራ ያበቅላል ወገራን ላረሰው

የሚበላ አይጠፋም ለጠረጠረ ሰው

እንዲሉ ይመስላል ኢህአፓም ድርጅቱን ያሽመደመዱትን ጓያዎች ጨምሮ ብዙ አባላትን አብቅሏል። ኢህአፓ ጓያ አባላትን ማፍራቱ ብቻ ሳይሆን ስህተቱ ሽንብራውንም ባለመጠርጠሩ ይመስለኛል የሚበላውን ("በ" ሲጠብቅ) ቁጥር ሊያበዛው የቻለ። ከዚህ የኢህአፓ ስህተትም ነጻ ነኝ ለማለት ይመስላል መሃመድም ወሬ ነጋሪ ነኝ ብሎ ብቅ ያለው። ለመሃመድ የተሰወረው ሀቅ ግን በድርጅቱ ውስጥ ያለፍነው እኔም እርሱም ሁላችንም ኢህአፓዎች ነን። የጥፋቱም ይሁን የልማቱ ተጋሪዎች። ለጥፋቱ የድርሻ የድርሻችሁን አንሱ ብንባል ደግሞ መሃመድ ይማም በነበረው የስልጣን እርከን የሚደርሰው መስፈርት ከተራዎቹ አባላት ልቅና ይኖረዋል። እርሱ ግን ሁሉንም ጥፋት በአመራሩ ላይ ይደፈድፈዋል። ከዚህም አልፎ ኢህአፓ መፈጠር አልነበረበትም ይለናል። አንገት ለምን ተሰራ ቢባል መሃመድ ራስን ለመሸከም ካላለን በቀር አዙሮ የሚያይ አንገት ቢኖረው ዛሬ የሚደረድራቸውን ስህተቶች ያኔ ላመራሩ በነበረው ቅርበት ከመፈጸማቸው በፊት በመጠቀም እንዳይፈጸሙ ማድረግ ይችል ነበር። ግን አላደረገውም። ምናልባት ያላደረገው ያኔ ዕውቀቱም ችሎታውም ከሰው ቤት ሆኖበት ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ሁላችንም፦

አወይ የልጅ ነገር ጤፍ ይዠ በወንፊት

ልብ ወደ ኋላ እንጂ አይገኝ ወደ ፊት

ማለት እንድንችል ዛሬ አንድም በዕውቀት አለያም በዕድሜ ገፍተናል። እናም ያለፈውን ስህተት አበጥረን ለማውጣት ሰፊድ መሆን ላይቸግረን ይችላል። ነገር ግን የዛሬ አርባ ዓመት የተከናወነን ኩነት ዛሬ ላይ ሆነን አዋቂነታችንን ለማስመስከር በምናጮኸው የጭቃ ጅራፍ መልሰን የምንገርፈው እኛኑን ነው። በከንቱ መወነጃጀሉም ራሳችንን ቢያስገምተን እንጂ ተደናቂ አያደርገንም። መሃመድ ግን የዛሬ ዘመን ወዳጆቹን እነ ያሬድ ጥበቡን፤ እነ እንድሪያስ እሸቴንና ፈረንጆቹን እነ ጌሪ ጆንን ለማስደሰት ሲል የትናንት ጓዶቹን ሳያጥብ ሊቀብራቸው ወሬ ነጋሪ ሆኖ ተሰለፈ።

መሃመድ "የራሴን ታሪክ ለመጻፍ ለራሴ ቃል ስገባ፤ አንዳንድ ጊዜ አብዮት በምንለው ኩነት የጠፉትን ጓደኞችንም ታሪክ ጨምሬ ለመናገር ነበር"። (ገጽ 13) ይለናል። ለጥቆም "እኛ በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የምንገኘው፤ ከብርሃኑ እጅጉ፤ ከወልደ አብ ኃይሌና ከመዝገብነሽ (መዝጊ)፤ ከአብዩ፤ ከዮሃንስ ብርሃኔና ሌሎችን በምን ይሆን? ከጠቀስኳቸው የፓርቲው አመራሮች በቀር የቀረነው የኢትዮጵያን ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓን ) መልኩን፤ ቅርጹንና ሙሉ እድገቱን ያስገኘን ሰዎች አልነበርንም"። (ገጽ 13) በማለት ራሱን ከድርጅቱ ፈቀቅ አድርጓል። በዚህም አገላለጹ የኢህአፓን ማንነት የራሱን ትርጉም አከናንቦ ወሬ ነጋሪ ሆኖ ወጥቷል። ሀቁ ግን ኢህአፓን ኢህአፓ ያደረጉት አመራሮቹ ብቻ አይደሉም። አባላቱ ማገርና ጨፈቃ፤ ግድግዳና ውጋግራ ሲሆኑ አመራሮቹ ምሰሶ ሆነው ነበር ኢህአፓን ኢህአፓ ያደረጉት። በነገራችን ላይ ማንኛውም ድርጅት መሃመድ ሊዘይረን እንደሚሻው በአመራሩ ህልውና ብቻ እድገቱ አይገነባም።

የራሱን መጽሃፍ ሲያሞካሽም እንዲህ ይለናል። "ይህ መጽሃፍ እንደ ክፍሉ ታደሰ ያ ትውልድ (ከፍል አንድና ሁለት) የኢህአፓን ትርከት(story) ደራሲው እንደመሪነቱ በታየው መንገድ ያጠናቀረው አይደለም። የክፍሉ መጽሃፍ የራሱ ታሪክ (memoir) ወይም የግሉ የቀን ተቀን ማስታወሻው (journal) ፤ ባይሆንም ቅሉ ታሪክ ግን ሊባል አይችልም። እንደ ታሪክ አልተጻፈምና" ይለንናል። ወረድ ብሎም "ሌላው የዚያን ወቅት ታሪክ የሚተርክ መጽሃፍ ያነበብኩት የአንዳርጋቸው አሰግድን የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ነቅናቄ (መኢሶን) ታሪክ ነበር። ያንዳርጋቸው አሰግድ መጽሃፍ እንደ ክፍሉ ታደሰው መረጃ የሚያጥረው ሳይሆን በበቂ መረጃ የዳበረ መደብል ነው። መጽሃፉ በራሱ ዕውቀት ለጋሽ ከመሆን አልፎ ለታሪክ ተመራማሮዎችና ለተማሪዎች ስለዚያ ዘመን መማሪያነት ሊጠቅም ይችላል"።(ገጽ 14) እንዲህ አይነቱን የማይመስል ነገር የኃይንት ሰው ሲሰማ ዛፍስ ባየሽ እምባጮ ይለዋል። የመኢሶን ታሪክ ፉት ቢሏት ጭልጥ ነች። አንዳርጋቸው አሰግድ ከመኢሶን አድርባይ ታሪክ ለንባብ የሚበቃ ቁምነገር ማግኘት ቸግሮት የመጽሃፉን ገጾች የሞላው በድግግሞሽ መሆኑን መሃመድ ለማየት አልፈለገ እንድሁ እንጂ መጽሃፉ የሃስብ ድሪቶ ነው። የመኢሶን ታሪክ ቢበዛ እንኳ murder she wrote ከመሆን ያለፈ ትርጉም የለውም!! የኢህአፓ ታሪክ ግን ስንክ ሳር ነውና ተጽፎ አያልቅም። ከክፍሉ የተረፈውን ቆንጆት ብርሃንና ህይዎት ተፈራ ቀጥለውታል። ገናም ይቀጥላል። የሚኢሶን ታሪክ ግን የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ያንዳርጋቸው አሰግድ ድሪቶ ነች።

የሆነው ሁሉ ሆኖ ግን በየ ሰኔው እንደ ዕባብ ቆዳውን ለሚያወልቅ የክህደት አባውራ፤ መሃመድ ይማም የመኢሶን ታሪክ ቀርቶ የናዚዎች ታሪክም ማር ማር ቢለው አይደንቀኝም። ከገሙ አይቀር መግማማት ነው ተብሎ የለ? መሃመድም ይግማ። ለምን? ቢባል ለኛ ካልገማ ጣፋጩነቱን ለነርሱ መሸጥ አይቻለውምና። የመኢሶን ልሳን የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ከኢህአፓው ልሳን ከዴሞክራሲያ የተሻለ

ወቅታዊ ትንታኔ ይሰጥ ነበር። የመኢሶን ሰዎችም ከኢህአፓ አመራር የተሻሉ ነበሩ ሲልም ወሬ ነጋሪው ወሬ ነዝቷል።

ዴሞን በዲሞትፈር

"አቶ ኃይሌ ፊዳ፤ ይጎንጩ የገብስ ጠላ ነው ምንም አይሉትም" ያለው ብርቅየ የዕብር ሰው ማን ነበር? በመንግሥት ጋዜጦች ውረድ እንውረድ ተብሎ በተከፈተው የብዕር ጦርነት ብርሃኑ እጅጉንና ዮሃንስ ብርሃኔን እናስታውሳለን። በጎሕ ግንባር ከተሰለፉትም መሃመድ ይማም አንዱ ነበር። የዛሬውን አያድርገውና። ጎሕና ፀደይ መጽሄት በብዕር ሰይፍ ሲቀራደዱ፤ ሜዳ ላይ ከነወረቀቱ የተዘረረውን መሃመድ ይማም ማስታወስ አይፈልግም። ዛሬ ሌላ ሰው ሆኗልና የትናንቱን ማንነቱን እንደ ያዘ በዛሬዎቹ ወዳጆቹ መታየት አይፈልግም። የሰፊው ሕዝብ ድምጽ የዮሃንስ አረቡንና የጸጋየ ደብተራውን የሰላ ብዕር መቋቋም ሲያቅተው ነበር ዴሞን በዲሞትፈር ብሎ ወደ ቀይ ሽብር የተሸጋገረው። የመሃመድ ድፍረትም በመጠጥ ዋሻ ውስጥ እንደ ተደበቀ ጥሎት የሸሸው በዚህ ወቅት ነበር።

የመሃመድና የመኢሶን ትኩስ ፍቅር ግን በዚህ አልተቋጨም።"በቅርቡ" ይላል መሃመድ ይማም "እንከን አልበወን (fine) የአንዳርጋቸው አሰግድን የሚኢሶን ታሪክ አነበብሁ። አንዳርጋቸው በኢህአፓ ገዳይ አመራር ላይ ነጥቡን ሲመሰርት የመጀመሪያው ግድያ የተጀመረው በኢህአፓ ነበር" ይላል። "ፍቅሬ መርድን በመግደል"። (ገጽ 141-42)

ከእንጨቶች አንዱ ብሳና ይነቅዛልን? ሲል ብሳናን ይጠይቀዋል። ብሳናም መንቀዝን ለዕንጨቶች ሁሉ ማን አስተማራቸውና? ሲል መለሰለት። ወደ ኃላ ጥቂት ዓመታት በምናባችን ተጉዘን አውሮፓ ውስጥ እንግባ። መኢሶኖች ከነብርሃነ መስቀል በፊት የድርጅት አስኳል ነበራቸው። እነ ብርሃነ መስቀል አልጀሪያ ሲገቡ ኃይሌ ፊዳ ወደ አልጀሪይ ጎራ ብሎ አነጋገራቸው። ወደ አልጀሪያ አካሄዱ ዶሮ ለብልሃቷ ተንጋላ ትጠጣለች ዓይነት ነበር። እነ ብርሃነ መስቀል ካገርቤት የወጡት በቅርብ ስለነበር አወጣጣቸውም ድርጅት ለመፍጠር እንደሆነ የነ ኃይሌ ቡድን ጠርጥሯል። እናም ኃይሌ በብብቱ ሥር ሊይዛቸው ፈለገ። ብርሃነ መስቀልም ነገሩ ገብቶት እባብ ለዕባብ ይሄዳል ካብ ለካብ ሆነና ለመሆኑ በኢትዮጵያ አብዮት ለመፈንዳት ስንት ጊዜ የሚፈጅ ይምስልስሃል? ሲል ኃይሌን ጠየቀው። እርሱም ቢያንስ አሥር ዓመት ሲል መለሰለት። ብርሃነም ከሁለት ዓመት ካለፈ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል ሲል የንኃይሌን ከጭብጥ ሁኔታ መራቅ አጋለጠው።(የክፍሉን ያ ትውልድ ይመልከቱ) ይህች የመጀመሪያ ግንኙነት የሁለቱ ቡድኖች የመፈታተሻ ሜዳ ሆነችና ተለያዩ። ሁለቱም ወገኖች ለስምምነት ሳይበቁ ቀርተው በመጨረሻም የየበኩላቸውን ድርጅት መሰረቱ።

እነ ኃይሌ ከጀብሃ ጋር ግንኙነት እንዲመሰርት አንድ የኤርትራ ተወላጅ አባላቸውን ወደ ሶሪያ ይልካሉ። ሌሎች ሁለት አባሎቻቸውንም ከአገር ቤት የኤሉባቡርና የወለጋ ተወላጆች ወደ ሱዳን ያስገባሉ። ወደ ጀብሃ የተላከው ልኡክ ጀብሃ ገብቶ ቀረ። የነ ኃይሌ የትጥቅ ትግልም በዚሁ መክኖ ቀረ። መኢሶን ግን ሞክሮ ስለአልተሳካለት ኢህአ ፓን ጠመንጃ ነካሽ ማለት ጀመረ።

የነ በርሃነ ቡድንም ዘግየት ብሎ ከሻዐቢይ ጋር ግንኙነት ፈጥሮ ወደ አሲምባ የሚሄደውን ቡድን ለስልጠና ወደ ቤሩት ላከ። አንድ ቤሩት ዩኒቨርስቲ ይማር የነበረ የነ ኃይሌ ቡድን አባል ስማቸውን በዘርዝር ለነ ኃይሌ ያስተላልፋል። እነ ኃይሌም ከደርግ ጋር ተደራደርው ወደ አገር ቤት ከመግባታቸው በፊት የአሲምባውን አስኳል ለእጅ መንሻ ለደርግ ሰጡ። አንዳርጋቸው አሰግድ የመጀመሪያውን ግድያ የጀመረው ኢህአፓ ነው ሲል ይህን ሀቅ ቀብሮ መሆኑን መሃመድ ይማም ልብ ሊለው ይገባል።

ደርግም የመጀመሪያውን ግድያ የጀመረው የቀድሞ ሹማምንትን በመረሸን ነበር። ከነዚህ የድሮ ባለስልጣኖች ጋር መለስ ተክሌንና ረዘነን ጨምሮ አምስት ሰዎች ተገድለዋል። ከነዚህ ወስጥ ሦስቱ የኢህአፓ አባላት ነበሩ። በዚያው ዓመት ደግሞ ሰኔ ወር ላይ ሁለት የጅማ መምህራን ተቋም ምሩቃን ሽባባው ካሴና ታረቀኝ በጥምቀት በዓል ታቦት ስታጅቡ ፀረ- ደርግ ግጥም ስታቀነቅኑ ውላችኃል ተብለው ከታሰሩ በኃላ ተገድለዋል። በቢቸና አውራጃ ጎጃም ውስጥ በጥይት ተደብድበው የተገደሉት አርሶ አደሮችም የኢህአፓ ደጋፊዎች ናችሁ ተብለው ነበር። እዚህ ላይ ፍቅሬ መርድ ዶክተር ነበር የኢህአፓዎቹ ግን ጎርደንዲኖሶች ነበሩ ካልተባሉ ቀድመው የተገደሉት ኢህአፓዎች ነበሩ። የበርጌሶቹ ሞት የደሮ ሞት የዶክተሩ ሞት ግን የሰው ሞት ተድርጎ እንዲታይ መሃመድ ይማም ስለ ፍቅሬ መርድ አገዳደል የጻፈውን ስንመለከት መሃመድ ለሰው ልጆች ዕኩልነት ሲታገሉ የወደቁትን ሰማዕታት ደመ ከልብ ያደርጋቸዋል። አንዳርጋቸው አሰግድ የመጀመሪያውን ጥይት ያጮኸው ኢህአፓ ነበር የሚለውን "ዕውነታም" የገደል ማሚቶው መሃመድ ይማም ይገዛው እንደሁ እንጂ ማንም ለህሊናው የሚገዛ ሰው አይቀበለውም። መሃመድ ግን ዕውነትን ለማግኘት በመኢሶን ወጀድ ሲልከሰከስ ውርደትን እንጂ ከበሬታን ስለማያተርፍ ወደ ህሊናው እንዲመለስ አላህ ይርዳው። ዕውነትና መኢሶን ምን ጊዜም ሆድና ጀርባ መሆናቸውን መሃመድ ተገንዝቦ ወደ ኅሊናው ቢመለስ ነበር አመኔታን ማግኘት የሚችለው። የዓመኔታ ነገር ሲናሳ ደግሞ አብሮ የሚነሳ ሌላም ነገር አለ። የመሃመድ መታሰርና ከእስር ቤት ማምለጥ።

በቀይ ሽበር ወቅት አይደለም መሳሪያ ይዞ፤ ከቶውንም በቦምብ የደርግን ካደሬ አቁስሎ ወይም ገድሎ ለዚያውም የዞን ኮሚቴ አባል የነበረ ስየል (torture) ሳይፈፀምበት ቃል በመስጠት ብቻ የታለፈ የኢህአፓ አባል የመጀመሪያውና የመጨረሻው ሰው እኔ ነኝ ይለናል መሃመድ ይማም። መሃመድ የመጽሃፉን ሰፊውን ስፍራ የሸፈነው በጫቱ፤ በስካሩና በፍርሃቱ የልቃቂት ጉልጉል ነበር። ጫት ስካርና ፍርሃት የተርከቱ ልቃቂት እንዲሆኑ የመረጠውም አለ ነገር አይደለም። ባንድ በኩል የድርግና የመኢሶን ጠይት አለ። በሌላ በኩልም የአንጃው ጥይት አለ። ከሁለቱ ጋር የሚፋለመውም በዚያን ወቅት ደካማው ወገን ኢህአፓ ነበር።

መሃመድ ለመኢሶን የነበረውን አድናቆት አስምሮበታል። ለአንጃው የነበረውን ድጋፍም ቀደም ሲል በለሆሳስ ወደ ኋላ ግን በድፍረት ውግናዊነቱን በገጽ 213 አጉልቶ አሳይቶናል። ከነዚህ እንድምታዎች ተነስተን መሃመድ ይማም ቀደም ብሎ ከደርጉ ቀንደኛ ገዳይ ከሃጂ ጋር ውል ተፈጣጥሞ ነበር ለማለት እንደፍራለን። በውሉ መሰረትም ይመስላል ማታውኑ ከጣውላ ማምረቻው (furniture house) ቤት አብረውት የነበሩትን አስጨርሶ እርሱ ለወሬ ነጋሪ የተረፈ ሰው ሆኗል። የነዚህን ጓዶች ታሪክ ነው የነርሱንም ታሪክ ከእኔው ታሪክ ጋር ልተርከላቸው ዓልሜ ተሪኬን ለመጻፍ የተነሳሁት የሚለን። (ገጽ 13)

ወሬ ነጋሪው መሃመድ ይማም በጠራራ ፀሀይ ከሃጂ ዐይን "ተሰውሮ ያመለጠው" በነዚያ ጓዶች የሬሳ ክምር ተጠልሎ ሳይሆን አይቀርም። የመሃመድ ይማም ነብስ በእነዚያ ጎዶች መሳሂነት ተረፈች። የዛሬው የመሃመድ ይማም ስጋትም መነሾው ከአዲስ አበባ ከአንጃ ጋርሆኖ፤ መዳረሻው ግን ፍላደልፊያ ከመዝጊ ጋር ተቆራኝቶበት ነው ሲያባንነው የሚኖረው።

## መዝጊን ማን ገደላት?

ደህና ጀግና ገዳዩን ያስመሰግናል እንዲሉ በቀይ ሽብር ቋያ ተርመጥምጣ፤ በአሲምባ በርሃ ዱር ገደል አቆራርጣ አሜሪካ ምድር ላይ ስትደርስ በጠራራ ፀሀይ በቤቷ ውስጥ አካሏ ተበሳስቶ ተገደለች። የሺን ገንዘብ ብላው የሽን ወገን ግን ፍራው እንዲሉ ሆነና ብርሃኑ እጅጉ አጠገቧ ባለመኖሩ ትከሻዋ ሳስቶ ብቻዋን አገኟት። አብሮ አደጎቿም ከዷት። ይልቁንም የራሷሰዎች የሞቷ ተባባሪ ሆኑ። ያገሬ ልጆች የምትላቸውም እነ እንቶኔ በማይታዩ እጆቻቸው (unseen hands) ህይዎቷን አስቀጠፉት።

ሞት የሰውን ልጅ ህይዎት በጊዜአዊነት በያንዳንዱ ሰው ላይ ያሰቀመጠ ባለዕዳ መሆኑን መዝጊ ድሮውንም አላጣችውም ነበር። ነገር ግን ዕዳየን እከፍልበታለሁ ባለችው ስፍራና ጊዜ ሳይሆን ባላለመችው ቦታና ጊዜ ህይዎቷን መነጠቋ ነው አሟሟቷን አስከፊ ያደረገው። ይህ አሳዛኝ ህልፈቷ "ወገኖቸ" ትላቸው በነበሩ ሰዎች መቀነባበሩ ድግሞ አሟሟቷን የበለጠ ውስብስብና አሳዛኝ ያደርገዋል። ። አሟሟቷን ስንመለከተው ገዳይዋን ዕርካታ በለገሰ  መልኩ ነበር ግድያው የተከናወነው።

"Weeks before she died, Mezy told me that she received a disturbing phone call from a person who said he had just arrived in Philadelphia by train.  She was uneasy about the phone call that I remember"( ገጽ 214) ከመሞቷ ሳምንታት ቀደም ብሎ አሁን ገና በባቡር መጣሁ ካላት ግለሰብ ህሊናዋን የረበሸ የስልክ ጥሪ አግኝታ ነበር። ከስልኩ በኋላ እንደማስታውሰው ህሊናዋ ዕረፍት አልነበረውም። ያ ሰው ማን ነበር? ማነነቱን ለመሃመድ ነግራው ኖሮ እርሱም ስጋት ስላደረበት ይሆን ማንነቱን ሊነግረን ያልፈለገ? ያ ግለሰብ ይሆን ከወንድ ጓደኛዋ ጋር አሲሮ ደም የመለሰባት? ጌታቸው ማሩ በኢንተርዞኑ ቁጥጥር ስር አንዳለ ነበር የተገደለው። የመዝጊ ባል በርሃኑ እጅጉ ደግሞ የያኔው ኢንተርዞን አባል ነበር። ገታቸው ማሩ አካሉ ተቆራርጦ እንደ ተገደለ የህይዎት ተፈራን Tower in the sky ጨምሮ ሌሎች ህትመቶችም ጠቅሰውታል። የመዝጊም አካል እንደ ጌታቸው አካል ነበር አገዳደሉ። እናስ ዐይን ላጠፋ ዐይን፤ ጥርስ ለሰበረ ጥርስ እንዲሉ ይሆን አሟሟቷ?

ሁሉንም ጊዜ እስኪፈታው፡- የገደለን መግደል ነበረ ሥራቸው

ያልገደለን መግደል ማን አስተማራቸው? ብለን እንለፈው።

ኅዳር 2006

abraham3106@comcast.net